# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ምዝገባና የነዋሪነት መታወቂያ አገልግሎት አሰጣጥ

# የተሻሻለ መመሪያ ቁጥር 3/2010ዓ.ም

# <u>ክፍል አንድ</u>

# <u>ጠቅላላ</u>

1. **<u>አውጭው ባለሥልጣን</u>**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ኃላፊ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲን ለማቋቋም በወጣው ደንብ ቁጥር 63/2007 ዓ.ም አንቀፅ 30 ንዑስ አንቀፅ (1) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

2. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ መመሪያ ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ምዝገባና የነዋሪነትመታወቂያ አገልግሎት አሰጣጥ የተሻሻለ መመሪያ ቁጥር 3/2010›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **<u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **“ከተማ”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፣
2. **“ቢሮ”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ነው፤
3. **“ኤጀንሲ”** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲነው፤
4. **“ነዋሪ”**ማለትበከተማውሦስተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን በሆነው ወረዳ በግሉ በሰራው፣ ተከራይቶ፣ ተቀጥሮ፣ ወይም ተጠግቶ የሚኖርና መደበኛ የመኖሪያ አድራሻ ያለው ስለመሆኑ በወረዳ አስተዳደር ጽህፈት ቤት ተመዝግቦ የሚታወቅ ግለሰብ ነው፤
5. **“መደበኛ መኖሪያቦታ”** ማለት የወሳኝ ኩነትምዝገባ እና ብሄራዊ መታወቂያ አዋጅ ፯፻፷/፪ሺ፬አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ ፰ የተሰጠው ትርጓሜ የተገለጸው ሆኖ በከተማው ክልል ውስጥ ህጋዊየሆነ የግል ወይም የመንግስት ቤትን የተከራየ ወይም የግል ወይም የቤተሰቡ ወይም ያስጠጋው ሰው የመኖሪያ ቤት ያለበት አድራሻ ነው፤
6. **”የነዋሪዎች ምዝገባ”** ማለት በቅደም ተከተል እና መለያ ቁጥር መሰረት የሚከናወን የነዋሪዎችን መረጃ አግባብነት ባለው ቅጽና ኮምፒዩተር በተሟላ መልኩ መዝግቦና አደራጅቶ የመያዝ ሂደት ነው፤
7. **“የአካባቢ መለያ ቁጥር”** ማለትአንድ የከተማ ነዋሪ ለሚኖርበት ክፍለ ከተማና ወረዳ አድራሻ ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ መለያ ቁጥር ነው፤

8. **“የግል መለያ ቁጥር”** ማለት አንድ የከተማ ነዋሪ በሚኖርበት የአካባቢ መለያ ቁጥር መነሻነት በመመዝገቢያውና በኮምፒዩተር ላይ ተመዝግቦ በመታወቂያ ምስክር ወረቀቱ ላይ የሚጻፍ ምስጢራዊ ቁጥር ነው፤

9. **“ሠራተኛ”** ማለት በኤጀንሲው፣ በክፍለ ከተማና በወረዳ ወሣኝ ኩነት ምዝገባና ኤጀንሲ በመንግሥት ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ በክብርመዝገብ ስራዎች የነዋሪዎች ምዝገባና መታወቂያ አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያ ነው፤

10. **“የቤተሰብ ተጠሪ”**ማለት ባል ወይም ሚስት ወይም በህግ ወይም ሌላ በውክልና ቤተሰብን የሚያስተዳድር የቤተሰብ አባል ነው፤

11. **“የነዋሪነት መታወቂያ ”** ማለት በከተማው ውስጥበመሰረተው መደበኛ የመኖሪያ አድራሻ በመኖሪያ አካባቢው ተለይቶ መለያ ቁጥር ተሰጥቶት ለአንድ ነዋሪ የሚሰጥ የነዋሪነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትነው፡፡

12. **“ካምፕ”** ማለት የሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላት፣ የፌዴራልና የአዲስ አበባ ፖሊስ ሠራዊት አባላት፣ ስደተኞችና መሰል ዜጎች በጋራ የሚኖሩበት በርከት ያሉ መኖሪያ ቤቶች ወይም ክፍሎች የያዘ ግቢነው፡፡

13. **“ጊዜያዊ መጠለያ”** ማለት ለተወሰነ የልማትና ማህበራዊ አገልግሎት ተብሎ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የተገነባ የጎዳና ተዳዳሪዎች ለተሀድሶና ስልጠና የሚቆዩበት ማዕከል፣ የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች የክህሎት ስልጠና እስኪጨርሱ የቆዩበት ማዕከላትና የመልሶ ማልማት ተነሺዎች የሚቆዩበት ጊዜያዊ ቤቶች ናቸው፤

14. **“ጥገኛ”** ማለት የራሱ መደበኛ ቦታ የሌለው ነገር ግን በነዋሪነት ከተመዘገበው ሰው ጋር ተጠግቶየሚኖርና በዚህ ሰው መደበኛ መኖሪያ ቦታ የሚታወቅ ግለሰብ ነው፤

15. **“አሰሪ”** ማለት አንድን ሰው በቋሚነት ወይም በጊዜያዊ ውል ቀጥሮ የሚያሰራ ሰው ነው፤

16. **“ ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው **አካል ነው፤**

17. **“ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት”** ማለት በክፍለ ከተማና በወረዳ ደረጃ የተቋቋመ ለኤጀንሲው ተጠሪ የሆነ ጽህፈት ቤት ነው፣

18. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ያካትታል ፡፡

4. <u>**የተፈፃሚነት ወሰን**</u>

***ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ በነዋሪነት ምዝገባ እና የነዋሪነት መታወቂያ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡***

## ክፍል ሁለት

## ስለ ምዝገባ

5. **ስለምዝገባ**

1. ማንኛውም ነዋሪ በመደበኛ መኖሪያ ቦታው አካባቢ በሚገኝ በወረዳ ወሣኝ ኩነትና ምዝገባ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቀርቦ በነዋሪነት መመዝገብ አለበት፡፡
2. ከ18ዓመት በታች የሆኑ ልጆችን አባት ወይም እናት ወይም ልጆችን በህግ የማሳደር ወይም የመንከባከብ ስልጣን ያገኘ የቤተሰብ ተጠሪ የተወለዱ ህፃናትን ጨምሮ ወይም ህጋዊ ውክልና የተሰጣቸው ተወካዮች በተወከሉበት ቤት እንደባለቤቱ ሆነው የሚያስተዳደሩትን ሰዎች በነዋሪዎች ቅፅ ላይ የማስመዘገብ ግዴታ አለባቸው፡፡
3. መስፈርቱን አሟልቶ በነዋሪነት ለመመዝገብ የሚቀርብ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ነዋሪ የሚከተሉትን መረጃዎችአሟልቶ መቅረብ አለበት፡-

    ሀ.ሙሉ ስም ከነአያት፣

    ለ.የእናት ሙሉ ስም፣

    ሐ.የትውልድ ቀን፣ወር፣ ዓመተ ምህረት፣

    መ.የትውልድ ቦታ ፣

    ረ. መደበኛ የመኖሪያ ቦታ፣

    ሠ. 2በ2 የሆነ ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣

    ሸ. የጋብቻ ሁኔታ፣

    ቀ. የስራ ሁኔታ፡፡

4. በነዋሪነት ለምዝገባ የሚቀርብ ሰው ከሌላ አካባቢ ቀይሮ የመጣ ከሆነ ከላይ ከተገለጸው መረጃ በተጨማሪ ቀድሞ ከሚኖርበት ቀበሌ/ወረዳ አስተዳደር የተሰጠው 6ወር ያላለፈው መሸኛ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፤ መሸኛው የሚከተሉትን መረጃዎች ማሟላት አለበት፡-

    ሀ/ሙሉ ስም ከነአያት፣

    ለ/ የእናት ስም፣

    ሐ/ የጋብቻ ሁኔታ፣ ያገባ ከሆነና ልጆች ካሉት የባለቤቱ ስም ከነልጆቹ፣ እንዲሁም ሌሎች አብረውት የተሸኙ የቤተሰቡ አባላት ስም ዝርዝር መካተት ይኖርበታል፤

    መ/ የትውልድ ዘመን ቀን፣ ወር፣ዓመተ ምህረት፣

ሠ/የትውልድ ቦታ፣

ረ/የመሸኛው ቀንና ቁጥር እንዲሁም ከ18 ዓመት በላይ የሆኑትንበፎቶግራፍ
የተደገፈ መሆን አለበት፤ፎቶግራፉ 6 ወር ወዲህ የተነሱት መሆን አለበት፤

ሰ/ መሸኛውንየሰጠው ህጋዊ አካል ወይም ባለስልጣን ወይም ባለሙያ ሙሉ ስምና የኃላፊነት
ማዕረግ የተቋሙ ማህተም ራስጌና ግርጌ ላይ ያረፈበት መሆን አለበት፤

ሸ/ መሸኛው ላይ የለቀቀበት ምክንያት መገለፅ አለበት፤

ቀ/ ይኖር የነበረበትን አድራሻክልል፣ዞን፣ወረዳ፣ቀበሌ፣የቤት ቁጥር መግለፅ አለበት፤

በ/ መሸኛው ላይ ያልተሟሉ ነገሮች ካሉ ሌሎች ህጋዊ መረጃዎች በማቅረብ እና በቃለ መሐላ
መረጋገጥ አለበት፤

5. በወረዳው በነዋሪዎች ቅጽ ተመዝግቦ ያለ ኢትዮጲያዊ ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ ሆኖ ከሌላ አካባቢ የቀየረ ሳይሆን በወረዳው ነዋሪ የነበረ ከሆነ ስለማንነቱ የሚገልጽ በፎቶግራፍ የተደገፈ ማስረጃ ወይም የትምህርት ማስረጃዎችን በማቅረብ እና ቃለ-መሐላ በመግባት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) መሰረት መመዝገብ ይችላል፡፡
6. ከክልሎች ወደ አዲስ አበባ ገብቶ ነዋሪ የሆነና ቋሚ አድራሻ ካለው ከኖረበት ክልል መሸኛ ማቅረብ የማይችል ከሆነና 6 ወርና ከዚያ በላይ በወረዳው ውስጥ ከቆየ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4/ሀ/ እና /በ/ን በማሟላት መመዝገብ ይኖርበታል የሚለው እንደተጠበቀ ሆኖ መሸኛ ማቅረብ የማይችልበትን አሳማኝ ማስረጃከወረዳው ዋና ስራ አስፈፃሚ ማቅረብ አለበት፡፡
7. ህጋዊ ውክልና የተሰጠው ተወካይ ወካይ በግል ቤቱ የነዋሪነት ቅፅ ከከፈተ በኋላ በተሰጠው የማሰመዘገብ ውክልና መሰረት ከራሱ በስተቀር እንደ ወካይ ሆኖ ሌሎች በወካይ ቤት ውስጥ የሚኖሩትን በተከፈተው የነዋሪነት ቅጽ በአንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 4 የተዘረዘረውን ሲያሟላ ማስመዝገብ ይችላል፡፡
8. ከሚኖርበት አካባቢ መሸኛ ያመጣና በቤቱ ውስጥ የሚኖር ከሆነ በተሰጠው ውክልና መሰረት ፋይል በመክፈት መመዝገብና አገልግሎት ማግኘት ይችላል፡፡
9. ለምዝገባ የሚቀርበው ሰው ከሁለት ዓመት በላይ በውጭ አገር ቆይቶ በቋሚነት ለመኖር የመጣ ከሆነ በሚያቀርበው የታደሰ ፓስፖርት ወይም ከዜግነት ጉዳይ መምሪያ ዜግነቱን አለመቀየሩን የሚገልፅደብዳቤ ሲያመጣ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በሚኖርበት ቤት አድራሻ ይመዘገባል፤

10. ከውጪ ሀገር የመጣ ከሆነ ከነበረበት ሀገር ኤምባሲ ወይም ኢምግሪሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መመሪያ በቋሚነት ተጠቃሎ የመጣ መሆኑ ሲረጋገጥ ይስተናገዳል፡፡

6. <u>ስለ ምዝገባ ቅፆች</u>

የምዝገባ ቅጾች የዚህ መመሪያ አንድ አካል ሆነው አባሪ የተደረጉ ሲሆን የሚከተሉትን ይይዛሉ፡-

1. በግሉ ወይም በቤተሰቡ ቤት የሚኖር የወረዳው ነዋሪ የሆነ ሰው የሚመዘገብበት የከተማው ነዋሪዎች ምዝገባ ቅፅ 001 ላይ ይሆናል፤
2. በቤቱ ውስጥ አከራይቶ ወይም በጥገኝነት የሚያኖረውን ግለሰብ መታወቂያ እንዲሰጠው ሲያስመዘግብ እና ግዴታ ቅጽ ሲሞላ አስመዝጋቢውም መዝጋቢ ፈፃሚውም በፊርማ ማረጋገጥ አለባቸው፤
3. እያንዳንዱ ቅጽ ስለተመዝጋቢውሰው የተሟላ መረጃ በሚይዝበት ሁኔታ ይደራጃል፤
4. እያንዳንዱ ቅፅ በጥራዝ የተከፋፈለ፣ 500 ገፅ ያለው፣በእያንዳንዱ ገፅ ፊትና ጀርባ የአንድ ቤተሰብ አባላት ስም ዝርዝር በመጠይቁ መሰረት የሚያስፈልጉ መረጃዎች የሚሞላ ይሆናል፤
5. በማንኛውም የነዋሪዎች መመዝገቢያ ቅጽ ላይ ሲመዘገብም ሆነ ከምዝገባ በኋላ ምንም ዓይነት ስርዝ ድልዝ ሊኖርበት አይገባም፡፡

7. <u>መደበኛ የመኖሪያቦታቸው በኪራይ፣በጥገኝነት፣በወታደራዊ እና ሰቪል ካምፕ የሆኑ ነዋሪዎች ስለመመዝገብ</u>

1. መደበኛ የመኖሪያ አድራሻቢኖራቸውም ከክልል ሲመጡ መሸኛወይም መታወቂያያልነበራቸውና ለረጅም ጊዜ ከኖሩ በኃላ መታወቂያና ሌሎች አገልግቶችን ለማግኘት ባለመቻላቸው በነዋሪነት ቅጽ ለመመዝገብ የጠየቁ ነዋሪዎች በተለያዩ ምክንያት ከሚኖርበት ክልል ሄደው መሸኛ ለማምጣት እንደማይችሉ በማስረጃ የተደገፈ አሳማኝ ምክንያት ስያቀርቡና እና መደበኛ መኖሪያ ቦታቸው የሚታወቅ መሆኑን ጠቅሶ የወረዳው ዋና ስራ አስፈፃሚ በፅሁፍ ሲያረጋግጥ ይስተናገዳሉ፡፡
2. በከተማ ውስጥ በተለያየ ቦታ የግል መኖሪያ ቤት ያለው የቤት ባለንብረት በቤቱ ውስጥ በኪራይ ወይም በጥገኝነት የሚያኖራቸውን በነዋሪነት ማስመዝገብ ቢፈልግ የታደሰ

የነዋሪነት መታወቂያ እና የቤት የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታና ፕላን ፎቶ ኮፒ በማያያዝ በማህተም የተደገፈ ደብዳቤ በማምጣት ተከራዮችን ወይም ጥገኞችን ማስመዝገብ ይችላል፡፡

3. ከላይ የተገለጸው ቢኖርም የቤቱ ባለቤት ራሱ በቤቱ ለመኖርና በነዋሪነት መመዝገብ ከፈለገ ከሚኖርበት አካባቢ መሸኛ በማምጣት መመዝገብ ይችላል፡፡
4. ከግለሰብ ቤት ተከራይቶ የሚኖር ወይም ተጠግቶ የሚኖር አከራዩ ወይም አስጠጊው ወይም አሳዳሪው በአካል ቀርቦ ተመዝጋቢው መሸኛ ማምጣት የማይችል መሆኑን በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ወይም በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 በተጠቀሰው መሰረት በማረጋገጥ በቤት ቅፅ ውስጥ እንዲመዘገብና መታወቂያ እንዲያገኝ ፍቃደኛ መሆኑን በጽሁፍ እና በቃለ-መሀላ ካረጋገጠ ይስተናገዳል፡፡
5. በአረጋውያንመጠሪያ፣በህፃናት ማሳደጊያ ተቋማትና ሌሎች ሰብአዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ለልማት ሰራዎች ሲባል በመንግስት ተፈቅደው በተከፈቱ ጊዜያዊ ካምፕና መጠለያዎች ውስጥ የሚገኙትን ነዋሪዎች ለመኖሪያነት የሚገለገሉበትን ቤቶች ተጠቅሶ ተቋማቱን ከሚመራው ክፍል ደብዳቤ ሲያቀርቡ ቃለ-መሀላ ገብተው እንደመደበኛ መኖሪያ ተወስዶ ይመዘገባሉ፡፡
6. ወታደራዊ ካምፕ ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎች ወታደራዊ ካምፑ ከሚያስተዳድረው ክፍል በሚፃፍላቸው ደብዳቤ እና የወረዳውአስተዳደር ካምፑ መኖሩን ሲያረጋግጥ የምዝገባ ቅፁን ተሞልቶ አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፡፡
7.መታወቂያ ለማሳደስ በሚመጡበት ወቅት በካምፑ ውስጥ ስለመኖራቸው ከካምፑ አስተዳዳሪ ወይም ሀላፊ በደብዳቤ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፤
8. በተለያየ ምክንያት ካምፑን በሚለቁበት ወቅት ግሰለቡ ስለመልቀቁ ካምፑ / ድርጅቱ/ በሁለት ወር ወይም በ60 ቀናት ውስጥ ለወረዳው ፅ/ቤት በደብዳቤ ማሳወቅ አለበት ፤

8. **የኮምፒዩተር ምዝገባ**

1. አንድሰው በዚህ መመሪያ መሠረት አግባብነት ካለው የነዋሪ መመዝገቢያ ቅጽ በተጨማሪ በኮምፒዩተር በተዘጋጀው ሶፍት ዌር ላይ ይመዘገባል፤
2. አንድ ሰው በኮምፒዩተር ሲመዘገብ የእጅ ወይም የአይን አሻራውን መስጠት አለበት፤

3. በሁሉም የከተማው ወረዳዎች የሚገኙ የነዋሪዎች መመዝገቢያ ኮምፒዩተሮች በመረጃ መረብ የተያያዙ ይሆናሉ፡፡
4. አንድሰው በኮምፒዩተር ለመመዝገብ ሲቀርብ በሚሰጠውየእጅ ወይም የአይን አሻራ መሠረት በከተማው ክልል ውስጥ በሌላ ወረዳ የተመዘገበ መሆኑ ከተረጋገጠ በመጀመሪያ ከተመዘገበበት ወረዳ መሰረዙን የሚገልጽ የመሸኛ ደብዳቤ እስካላቀረበ ድረስ መመዝገብ አይችልም፡፡
5. በእነ የተከፈቱ ፋይሎችን በሚመለከት ፋይል የሚያንቀሳቅስ ተጠሪ በጋራ ወክለው ወይም በየራሳቸው አስፈላጊውን አገልግሎት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

<u>ክፍል ሦስት</u>

<u>ስለ ነዋሪነት መታወቂያ</u>

9. <u>የነዋሪነት መታወቂያ ይዘት</u>

1. የነዋሪነት መታወቂያ በኤጀንሲ አማካይነት በጥንቃቄና ምስጢራዊነቱን ጠብቆ የሚታተም ሆኖ የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

ሀ. ስም ከነአያት፣

ለ. የእናት ሙሉ ስም፣

ሐ. የትውልድ ቦታ፣

መ. የትውልድ ዘመን፣ ቀን፣ወርና ዓመተ ምህረት፣

ሠ. ፆታ፣

ረ. መደበኛ የመኖሪያ አድራሻ፡- ክ/ከተማ፣ ወረዳ፣ የቤት ቁጥር፣ሌላ አድራሻ ካለ፣

ሰ. የስራ ሁኔታ፣

ሸ. በአደጋ ጊዜ የቅርብ ተጠሪ ስም አድራሻ፣ የመ/ቤት ወይም የመኖሪያ ቤት ስልክ ቁጥር ወይም የሞባይል ስልክ፣

ቀ. የመዝገብ ቁጥር፣

በ. ብሔር፣

ተ. ዜግነት፣

ቸ. መታወቂያ የተሰጠበት ቀን፣ወር፣ዓ.ም እና የአገልግሎት ዘመኑና አገልግሎቱ የሚያበቃበት ቀን፣

ነ. መታወቂያ የሰጠው ባለሙያ ስም፣ኃላፊነትና ፊርማ

2. የነዋሪነት መታወቂያ ከላይ ከተገለፁት ዝርዝር ሁኔታዎች በተጨማሪ

ሀ. የቅፁን፣የጥራዙንና የገፁን ቁጥር፣

ለ. በተመዘገበበት ቁጥር ላይ የተሰጠውን ተራ ቁጥር እና በአካባቢ መለያ ቁጥር መነሻነት የሚሰጥ መለያ ቁጥር መያዝ አለበት፡፡

3. አንድ የነዋሪነት መታወቂያ ለሁለት ዓመት ያገለግላል፡፡

## 10.የነዋሪነት መታወቂያ አሰጣጥ

1. በሚኖርበት ወረዳ በነዋሪዎች ምዝገባ ቅጽ ላይ የተመዘገበ ሰው ስለማንነቱ የሚገልጽ የነዋሪነት መታወቂያ እንዲሰጠው የመጠየቅ መብት አለው፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥያቄ የሚያቀርብ ሰውበወረዳውጽ/ቤት በአካል ቀርቦ ከ6ወር ወዲህ የተነሳውን 2 ጉርድ ፎቶግራፍ በመያዝና የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት አገልግሎቱን ያገኛል፤
3. መታወቂያ በውክልና አይሰጥም፤ አይታደስም፣
4. ተወካይ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 7 እና 8 መሰረት የተመዘገበ ከሆነ የነዋሪነት መታወቂያ ማግኘት ይችላል፤ በስሩ የሚያስተዳድራቸውንም ግለሰቦች እና ተከራዮች መታወቂያ እንዲሰጣቸው ያደርጋል፡፡
5. የነዋሪነት መታወቂያ የተሰጠው ነዋሪ መታወቂያው የሚያስገኘውን መብትና ጥቅም ያገኛል፣
6. በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያንና የውጭ ሀገር ዜጎችየነዋሪነት መታወቂያ አይሰጣቸውም፤
7. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት በነዋሪነት የተመዘገበ በውጭ ሀገር ሲኖር የነበረ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን አለመቀየሩንና በነዋሪነት በከተማው መኖሩ ተረጋግጦ የመታወቂያ አገልግሎት ሊሰጠው ይችላል፣
8. የነዋሪነት መታወቂያ የሚጠይቅ ማንኛውም ግለሰብ በወረዳው ውስጥ በመደበኛነት ነዋሪ የሆነ ማለትም የግል መኖሪያ ቤት ያለው ወይም የመንግስት ቤት የተሰጠው ስለመሆኑ ቤቱን ከሚመለከተው አካል ጋር የተዋዋለበትን ውል በማቅረብ ፤ የግሉ ከሆነ የቤቱን ሰነድ በማሳየት የነዋሪነት መታወቂያውን ያገኛል፡፡

## 11. የነዋሪነት መታወቂያንስ ለማደስና ምትክ ስለመስጠት

1. በዚህ መመሪያ መሠረት ነዋሪነት መታወቂያ የተሰጠው ማንኛውም ነዋሪ የነዋሪነት መታወቂያ እስከ ሁለት ዓመት የሚያገለግል ሆኖ የአገልግሎት ዘመን ሲያበቃ መታወቂያው ተመላሽ ሆኖአዲስ መታወቂያ ይሰጠዋል፡፡

2. የተሰጠው መታወቂያ የተቀደደበት ወይም የተቃጠለበት ወይም የተበላሸበት በሌላ ማንኛውም ምክንያት ከጥቅም ውጭ ሲሆንበት ወዲያውኑ ለሰጠው አካል በጹሁፍ ሲያመለክት እና በቃለ-መሀላ ሲያረጋግጥ ምትክ መታወቂያ ይሰጠዋል፡፡
3. መታወቂያ የጠፋበት የወረዳው ነዋሪ ስለመጥፋቱ ከአካባቢው ፖሊስ ፅ/ቤት ማስረጃ ካመጣና በነዋሪነት ቀጽ ላይ መመዝገቡን ከተረጋገጠ በኋላ እንዲሁም በቃለ መሀላ በማረጋገጥ በምትኩ የነዋሪነት መታወቂያ ይሰጠዋል፤
4. ማንኛውም በዚህ መመሪያ የነዋሪነት መታወቂያ የተሰጠው ነዋሪ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤቱ በአካል በመቅረብ መታወቂያውን ማደስ ይኖርበታል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 እንደ ተጠበቀ ሆኖ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያላደሰ ነዋሪ የተሰጠውን መታወቂያ በአካል በጽ/ቤቱ ቀርቦ በወረዳው እየኖረ ስለመሆኑ በቃለ መሐላ ተረጋግጦተቀጥቶ ይታደስለታል፤
6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 እና 3 ምትክ የነዋሪነት መታወቂያ የሚይዘው ቁጥር የቀድሞውን የመታወቂያ ቁጥር ይሆናል፡፡
7. ከዚህ በፊት በወረዳው ዋና ስራ አስፈጻሚ አማካኝነት ነዋሪ ነው ተብሎ በ00 እና XX በሚል የተሰጠ የነዋሪነት መታወቂያ ግለሰቡ አሁንም በወረዳው እየኖረ ስለመሆኑ ከወረዳው ዋና ስራ አስፈጻሚ ደብዳቤ ይዞ በመምጣት መታወቂያውን ማሳደስ ይችላል፡፡

12.<u>የሰነድ አልባ ባለይዞታዎችን መታወቂያ መስጠት በተመለከተ</u>

1. የሰነድ አልባ ባለ ይዞታዎች እና አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ የተያዘ ይዞታ መብት የሚፈጠርለት መሆኑ የተረጋገጠና በወረዳው የሚኖሩ መሆናቸው ሲረጋገጥ የነዋሪነት መታወቂያ እንዲሰጣቸው ተደርጎ ከሚመለከተው አካል ማረጋገጫ ሲሰጥ ህገ-ወጥ ሆነው ከተገኙ እና አግባብ ባለው አካል ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ መታወቂያ አገልግሎት አይሰጥም እድሳትም አይደረግም ቀድሞ ያገኘው የነዋሪነት መታወቂያውም የሚነጠቅ ይሆናል፤
2. የሰነድ አልባ ባለይዞታዎች መሆናቸውን የተረጋገጠ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦች በዚህ አንቀፅ 1 በተገለፀው መሰረት ዕድሜቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ የመታወቂያ አገልግሎት ያገኛሉ፡፡

13.<u>**የነዋሪነት መታወቂያ በንግድ ቤት አሰጣጥ በተመለከተ**</u>

1.በማንኛውም ንግድ ቤት የነዋሪነት መታወቂያ አይሰጥም፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተገለፀው ቢኖርም የንግድ ቤቱና የመኖሪያ ቤቱ በአንድነትስለመሆኑ ቤቶች ልማት ጽ/ቤት ወይም ከግብር ከፋዮች ጽ/ቤት በሚያቀርቡት ማስረጃ መሰረት የነዋሪነት መታወቂያ ያገኛሉ፡፡

3. ሙሉ ለሙሉ ቤቱ ወደ ንግድ ቤት የተዛወረ ከቤቶች ልማት ጽ/ቤት ማስረጃ ከቀረበ የነዋሪነት መታወቂያ አያገኝም፡፡

## ክፍል አራት

## ሌሎች አገልግሎቶች

14. ያላገባ የምስክር ወረቀት ለጋብቻ እንደ ደጋፊ ማስረጃ የሚያገለግል ሆኖ የሚሰጥ ሳይሆን የተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት ለሚጠይቁ ተገልጋዮች ብቻ የሚሰጥ ሆኖ፡-

1. ያላገባ/ች/ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ተገልጋዮች ማሟላት የሚገባቸው፡-

ሀ. ጋብቻ ያልፈፀሙ ስለመሆኑ ከነዋሪነት መመዝገቢያ ቅጽ ላይ ተረጋግጦ በተጨማሪም ቃለ መሃላ መፈፀም፤

ለ. ከ6 ወር ወዲህ የተነሱት 2 ፓስፖርት ሳይዝ ጉርድ ፎቶ ግራፍ፤

ሐ. የጠያቂው የታደሰና ሙሉ መረጃ የያዘ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት፤

መ. ጥያቄው የቀረበው በውክልና ከሆነ ልዩ ውክልና ማስረጃ የወካይ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም ትራቭል ዶክመንት ወይም የስደተኛ መታወቂያ ኮፒ የተወካይ የታደሰ መታወቂያ በማቅረብ ይስተናገዳሉ፡፡

ሠ. በወረዳ ጽህፈት ቤት የሚሰጠው ያላገባ የምስክር የሚያገለግለው ለ6 ወር ብቻ ነው፡፡

ረ. ፍቺ ከፈጸሙ ወይም ባለቤታቸው ከሞቱ ወይም ከጠፉ ያላገቡ መሆናቸውን ማስረጃ ሲፈልጉ በፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ ካስወሰኑ በኋላ የፍቺ ውሳኔውን ኮፒ በማያያዝና ቃለ መሃላ በመፈፀም ፍቺ ከፈፀሙ በኋላ ያላገቡ ስለመሆናቸው ያላገባ ማስረጃ ይሰጣቸዋል፤

ሰ. ጋብቻ ከፈፀሙ በኋላ ከጋብቻ በፊት ያላገቡ መሆናቸውን ማስረጃ እንዲሰጣቸው ከጠየቁ የጋብቻ ማስረጃቸውን በማቅረብና ቃለ መሃላ በመፈፀም ጋብቻ እስከ ከፈጸሙበት ድረስ ቀን፣ ወር፣ ዓ.ም ተገድቦ አገልግሎቱን ያገኛሉ፤

ቀ. የነዋሪነት ምዝገባ በሚከናወንበት ወቅት በነዋሪነት ምዝገባ ቅጽ ላይ ያገባውን ያላገባ እንዲሁም ያላገባውን ያገባ በማለት የተመዘገበውን በስህተት መመዝገቡን ጉዳዩን በሚያውቁ በሶስት ምስክሮች በማስመስከር እና በተጨማሪም በቃለ መሃላ ሲያረጋግጥ ትክክለኛውን ማስረጃ እንዲሰጥ ይደረጋል፤

2. ከኢትዮጲያ ውጪ የሚኖሩ ኢትዮጲያውያንና ትውልድ ኢትዮጲያውያን ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በተመለከተ፡-

ሀ. ከኢትዮጵያ ውጪ የሚኖሩ ኢትዮጲያውያን ትውልደ ኢትዮጲያውያን ከኢትዮጲያ እስከወጡበት ዘመን ድረስ ሲኖሩበት ከነበረው ወረዳ ከነዋሪዎች መመዝገቢያ ቅፅ ላይ በማገናዘብ ያላገቡ መሆናቸውን የሚገልፅ መረጃ ካለ እሱን መነሻ በማድረግና በተጨማሪም ቃለ መሃላ በመፈፀም ማስረጃ ያገኛሉ፤ ማስረጃው ከኢትዮጲያ እስከ ወጡበት ቀን ድረስ ተገድቦ የሚወጣ ሲሆን የሚያቀርቡት ማስረጃ ቀን፣ ወርና ዓ.ም ያልተሟላ ከሆነ በቃለ መሃላ እንዲረጋገጥ ይደረጋል፤

ለ. ከውጭ ሀገር በተላከ ውክልና የሚጠየቅ ከሆነ የተላከው ውክልና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በሰነዶች ማረጋገጫ ጽ/ቤት መመዝገብና መረጋገጥ አለበት፤

ሐ. ኢትዮጲያ ውስጥ እስከ ነበሩ ድረስ ያላገቡና ውጭ በነበሩበት ወቅት ያላገቡ መሆናቸውን የሚገልፅ ማስረጃ ያቀረቡ በጥቅሉ ያላገቡ የሚል ማግኘት ይችላሉ፤

መ. ከሁለት ዓመት በታች ለኮንትራት ስራወይም ለጉብኝት ወይም ለትምህርት ወደ ውጭ ሀገር የወጡ ኢትዮጲያውን ያላገባ ማስረጃ ሲጠይቁ በወረዳው የሚገኘውን የነዋሪነት መመዝገቢያ ቅፅ መነሻ በማድረግና ቃለ መሃላ በመፈፀም ማስረጃውን ያገኛሉ፤

ሠ. ተገልጋዩ የሰጠው መረጃ ወይም ማስረጃ እውነተኛና ትክክል መሆኑን በሚዘጋጀው ቅጽ በፊርማው ያረጋግጣል፡፡

15.<u>**የነዋሪነት ደብዳቤ ለሚጠይቅ፤**</u>

1.በነዋሪነት ቅፅ ላይ በነዋሪነት የተመዘገበ መሆን አለበት፡፡

2.የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ዋናውን እና ኮፒ ማቅረብ አለበት፡፡

3.የማመልከቻ ፎርም መሙላት እና መፈረም አለበት ፡፡

4.በወረዳውምን ያህል ጊዜ እንደኖረ ማስረጃ ከጠየቀ በግልፅ የነዋሪዎች ቅፅ ላይተመዝግቦ መገኘት አለበት፡፡ በተጨማሪም በቃለ-መሀላ ማረጋገጥ አለበት ፡፡

5.የነዋሪነት ማረጋገጫ ደብዳቤ በውክልናሲጠየቅ ህጋዊ የውክልና ሰነድ በማቅረብየወካይየታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ኮፒ ሲያቀርብ የተወካይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም የመንጃ ፍቃድዋናውን እና ኮፒ በማቅረብ ይስተናገዳሉ፡፡

16. <u>ቅጽ ላይ የተቀመጡ መረጃ የማግኘት መብት</u>

ማንኛውም በነዋሪነት የተመዘገበሰው ጥያቄውን ሲያቀርብ በተመዘገበበት ቅጽ ላይ የተቀመጡ መረጃዎችንግልባጭከነዋሪዎች መመዝገቢያ ቅጽ ላይ ተረጋግጦ ይሠጠዋል፡፡

17.<u>መሸኛ ደብዳቤ ስለመስጠት</u>

1. ጠያቂው ባለጉዳይ በግንባር መቅረብ አለበት፡፡
2. በነዋሪዎች ቅፅ ላይ ተመዝግቦ መገኘት አለበት፡፡
3. ከወረዳ የወሰደውን የነዋሪነት መታወቂያ መመለስ አለበት ፡፡
4. መሸኛውን የሚወስደው አካል በመንግስት ቤት የሚኖርና የቤቱተጠሪ ከሆነ የመንግስትን ቤት ስለማስረከቡ ከመንግስት ቤቶች ልማት ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡
5. ከስድስት ወር ወዲህ የተነሳው 4X4 መጠን ያለው ፎቶግራፍ ማቅረብ አለበት ፡፡
6. መሸኛው ከአንድ ሰው በላይ የሚሰጥ ከሆነ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑት ከ6 ወር ወዲህ የተነሱት 4X4 መጠን ያለው ፎቶግራፍ በማቅረብ፣ በቤተሰብ ዝርዝር መመዝገቢያ ላይ ሙሉ መረጃ ተመዝግቦ መላክ አለበት ፡፡
7. መታወቂያ ጠፋብኝ የሚል ከሆነ ከፖሊስ ስለመጥፋቱ ማስረጃ ወይም እሱነቱን የሚገልፅ በፎቶ ግራፍ የተደገፈ ማስረጃ በማቅረብ እና በቃለ-መሐላ በማረጋገጥ መታወቂያ ወይም መሸኛ ማግኘት ይችላል፡፡
8. በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው መሸኛ በውክልና ማስተናገድ የሚቻለው ወካይ መሸኛ እንዲያስፈጽምለት በግልጽ ሲወክለው ብቻ ነው፡፡
9. ከነዋሪነት መዝገብ በቤቱ ባለቤት እንዲሰረዝ የተደረገ ነዋሪ መሸኛ ማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

18.<u>ማንኛውም ደብዳቤዎች</u>

1.ለሀገር ውስጥ በቀጥታ በአድራሻ የሚፃፍ ሲሆን ለውጭ ሀገር ለሚመለከተው ሁሉ ተብሎወይም አድራሻ ተጠቅሶ ሊጻፍ ይችላል፡፡

2. ለፍርድ ቤት የሚፃፈው ማንኛውም መረጃፍርድ ቤቱ ሲጠይቅ ብቻ የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት
## ስለ ተግባርና ኃላፊነቶች

### 19.<u>የኤጀንሲ ተግባርና ሀላፊነት</u>

በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚነት ኤጅንሲው የሚከተሉትተግባርና ሀላፊነትይኖረዋል፡-

1) ለነዋሪዎች ምዝገባ አስፈላጊ የሆኑ ቅጾችን አንድ ወጥ በሆነ መንገድ ማሳተምና ለሁሉም ማሠራጨት፣
2. ለከተማው ነዋሪዎች አንድ ወጥ የሆነ የነዋሪነት መታወቂያ ምስጢራዊ በሆነና ለህገ-ወጥ ተግባር በማይጋለጥ መልኩ የማሳተምና በአግባቡ የማሰራጨት፣
3. የነዋሪዎች መመዝገቢያ የኮምፒዩተር ሶፍትዌር በወረዳዎች የመጫንና ደህንነቱን የመከታተል እንዲሁም ብልሽት ሲኖር የመጠገንና የማስተካከል፣
4. በየወረዳውየወሳኝ ኩነቶችቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የሚገኙ የነዋሪዎች መመዝገቢያ ኮምፒዩተሮችን ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር በመረጃ መረብ የማገናኘትና ደህንነቱን የመከታተል፣
5. ለነዋሪዎች የኮምፒዩተር ላይ ምዝገባ አሻራ የሚወሰድበትን ቁሳቁስ ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ማዘጋጀትና ደህንነቱን መከታተል፣
6. በማንኛውም ሁኔታ ከዚህ መመሪያ ውጪ የሆነ ህገ-ወጥ ተግባር ሲፈጸም ተከታትሎ ህጋዊ እርምጃ መውሰድና እንዲወሰድ ማድረግ፡፡

### 20.<u>የክፍለ ከተማ ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ተግባርና ሃላፊነት</u>

በሌሎች አግባብነት ያላቸው ህጎች የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚነትየሚከተለውተግባርና ኃላፊነትይኖረዋል፤

1. በኤጀንሲውእየታተሙ የሚሰራጩትን ለነዋሪዎች ምዝገባ አስፈለጊ የሆኑ ቅጾችንና የመታወቂያ ካርድ ከኤጀንሲው በህጋዊ የመረካከቢያ ቅጽ በመረከብ በስሩ ላሉ ወረዳዎች ማሰራጨት፣

2. የነዋሪዎች መመዝገቢያ የኮምፒዩተር ሶፍትዌር በወረዳዎች እንዲጫን ማድረግና ደህንነቱን የመከታተል እንዲሁም ብልሽት ሲኖር ለኤጀንሲውኢንፎርሜሽ ኮምኒኬሽን ቴክኖሎጂ ማሳወቅ፣
3. ለአገልግሎት አሰጣጡ አስፈላጊው የሰው ሃይል እንዲሟላ ጥያቄ ማቅረብና ተከታትሎ ማስፈጸም፣
4. ወደ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤትለሚገቡ አዲስ ሠራተኞች የስራስልጠና መስጠት፣
5. በማንኛውም ሁኔታ ከዚህ መመሪያ ውጪ የሆነ ህገ-ወጥ ተግባር ሲፈጸም ተከታትሎ ህጋዊ እርምጃ መውሰድና እንዲወሰድ ማድረግ አለበት፡፡

21.<u>የወረዳቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>

በሌሎች አግባብነት ያላቸውሕጎች የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚነትየሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነትይኖረዋል፡-

1. በኤጀንሲው እየታተሙ የሚሰራጩትን ለነዋሪዎች ምዝገባ አስፈለጊ የሆኑ ቅጾችንና የመታወቂያ ካርድ ከክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤትበህጋዊ የመረካከቢያ ቅጽ በመረከብ በስራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣
2. የነዋሪዎች መመዝገቢያ የኮምፒዩተር ሶፍትዌር በወረዳው እንዲጫንና ብልሽት ሲኖር ለክፍለ ከተማውቅርንጫፍ ጽህፈት ቤትየማሳወቅና ደህንነቱን የመከታተል፣
3. ለአገልግሎት አሰጣጡ አስፈላጊው የሰው ሃይል እንዲሟላ ጥያቄ ማቅረብና ተከታትሎ ማስፈጸም፣
4. ወደ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤትለሚገቡ አዲስ ሠራተኞች የስራ ስልጠና መስጠት፣
5. ከዚህ መመሪያ ውጪ የሆነ ህገ-ወጥ ተግባር ሲፈጸም ተከታትሎ ህጋዊ እርምጃ መውሰድና እንዲወሰድ ማድረግ እንዲሁም ለክፍለ ከተማውና ለኤጀንሲው ሪፖርት ማድረግ፡፡

22.<u>የወረዳ ፈጻሚ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. አግባብነት ባለው ቅፅና በኮምፒዩተር ነዋሪዎችን የመመዝገብ፣

2. የነዋሪዎችን መረጃ  በፋይል እንዲሁም በኮምፒዩተር በተገቢው አደራጅቶ የመያዝ፣ በተጠየቀ ጊዜ ለጠያቂው አካል የማቅረብ፣
3. የመታወቂያ ምስክር ወረቀት የወሰዱ ነዋሪዎችን ዝርዝር በየወሩ ለክፍለ ከተማውና ለኤጀንሲው በጽሁፍ (ሃርድ ኮፒ) እና በሶፍት ኮፒ እና በድህረ-ገጽ የተደራጀ መረጃ በሪፖርት የማስተላለፍ፤
4. ነዋሪዎች ለምዝገባም ሆነ ለመታወቂያ ጥያቄ ለማቅረብ የሚሞሉትን ፎርም አዘጋጅቶ ለተገልጋዮች የማቅረብ፤
5. የእያንዳንዱን ተመዝጋቢ መረጃ በጥንቃቄ ያለ ስርዝ ድልዝና ስህተት የመመዝገብ፤
6. ተመዝጋቢው ወይም መታወቂያ ጠያቂውበወረዳው ነዋሪ መሆኑን ወይም ተገቢውን ወቅታዊ የሆነ መሸኛ ማቅረቡን የማረጋገጥ፤

23.<u>የተመዝጋቢ ነዋሪ ኃላፊነትና ግዴታ</u>

1. ነዋሪ የሆነ ሰው ለመመዝገብ ወይም መታወቂያ ለመውሰድ ወደ ወረዳው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሲቀርብ ተገቢውን የተዘጋጀ ፎርም ሞልቶ መፈረም አለበት፤
2. ለምዝገባም ሆነ መታወቂያ ለመውሰድ ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው ራሱ በግንባር መቅረብ ይኖርበታል፤
3. በወረዳው ነዋሪ የሆነ እና እድሜው 18 ዓመት የሞላውና በህግ ችሎታ ያለው ሰው እራሱ በመዝጋቢው አካል ዘንድ በግንባር ቀርቦ አግባብነት ባለው መዝገብ ላይ መመዝገብ አለበት፤
4. በወረዳው ነዋሪ የሆነ እድሜው 18 ዓመትያልሞላው በወላጅ ወይም በሞግዚት ወይም በቤተሰቡ ተጠሪ አማካኝነት አግባብነት ባለው መዝገብ ላይ ይመዘገባል፤
5. ለምዝገባ የሚቀርብ ሰው ማንነቱን ሊገልጽ የሚችል በፎቶግራፍ የተደገፈ ህጋዊ ማስረጃ የማቅረብ ወይም በቃለ መሀላ ማረጋገጥ አለበት፡፡
6. ማንኛውም የተመዘገበ ነዋሪ ያስመዘገበው መረጃ በውልደት፣ በጋብቻ፣ በፍቺ እና በመሳሰሉት ሲለወጥ መዝጋቢው አካል ዘንድ ቀርቦ ያጋጠመውን ለውጥ ማስመዝገብ ይኖርበታል፤

7. አንድሰው በተለያየ ምክንያት የተመዘገበበትንና መታወቂያ የወሰደበትን ወረዳ ለቆ ሲሄድ ወዲያውኑ ለመዘገበውና መታወቂያውን ለሰጠው ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤትበማሳወቅ መታወቂያውን በመመለስ መሸኛ ይወስዳል፤
8. ባለመታወቂያውበዚያውወረዳ ውስጥ ኖሮ ሌላ የመኖሪያ አድራሻ የሚቀይር ከሆነ የአድራሻ ለውጥ (የቤት ቁጥር)ማሳወቅ አለበት፤
9. ማንኛውም ነዋሪ ለምዝገባም ሆነ መታወቂያ ለመውሰድ ለቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ ጥያቄ ሲያቀርብ ትክክለኛ የሆነ የቃልም ሆነ የሰነድ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## 24.<u>የቤትአከራይ መብትና ግዴታ</u>

1. አንድ ሰው ቤቱን በከፊል ወይም በሙሉ ያከራየ ወይም እንዲኖርበት የፈቀደ ከሆነ በቤቱ ነዋሪ የሆነውሰው በነዋሪዎች መመዝገቢያ ላይ እንዲመዘገብ ተገቢውን ድጋፍ የማድረግ ይችላል፤
2. የቤት አከራይ ወይም እንዲኖር የፈቀደ ሰው በቤቱ የሚኖረውሰው በዚህ መመሪያ መስፈርት መሠረት መታወቂያ እንዲያገኝ አስፈላጊውን ትብብር የማድረግ ግዴታ አለበት፤
3. አንድ የቤት ባለቤት ከአንድ በላይ በስሙ የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ቢኖረው የነዋሪነት መመዝገቢያ ቅጽ መክፈት የሚችለው በመደበኛ የመኖሪያ አድራሻው ስለሆነ በሌሎች ወረዳዎች ወይም ክፍለ ከተሞች ባሉት ተጨማሪ የግል ቤቶቹ የቤቱን ተከራዮች(ጥገኞች) ማስመዝገብ ይችላል፤
4. ለሀገር ደህንነትና ለህዝቦች ሰላም ሲባል ቤቱን ያከራየ የወረዳው ነዋሪ በቤቱ የሚያኖራቸውን ግለሰቦች ለወረዳው ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት በማሳወቅና እንዲመዘገቡ በማድረግ አገልግሎት እንዲሰጣቸው የማድረግ ግዴታ ያለበት ሲሆን ተከራዮች ቤቱን ለቀው ሲሄዱ ስለመልቀቃቸው በወቅቱ ለወረዳው ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ማሳወቅ አለበት ፡፡

## ክፍል ስድስት

## ስለ ቤተሰብ ተጠሪና እርማት

### 25.ስለቤተሰብ ተጠሪ

አግባብነት ባለው የነዋሪዎች ምዝገባ ቅፅ ጥራዝ ላይ የቤተሰብ ተጠሪ በሚለው ስፍራ፡-

1. በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ባልና ሚስት ያሉ ከሆነ በአንድነት የቤተሰቡ ተጠሪ ሆነው በመጠይቁ መሠረት የሁለቱም ስምና ተገቢው መረጃ ይመዘገባል፤
2. ከባል ወይም ሚስት አንዱ ብቻ ያለ በሚሆንበት ጊዜ ያለውሰውተጠሪ ሆኖ በመጠይቁ መሰረት ስምና መረጃው ይመዘገባል፤
3. ሌላ ተጠሪ በሚለው ስፍራ ልጆች፣ የልጅ ልጆቻቸው፣ ወደ ጐን የሚቆጠርዘመድ፣ ወንድምእና እህትበሚመዘገብበት ጊዜ አግባብነት ባለው የነዋሪዎች ምዝገባ ቅፅ ላይ ይመዘገባል፤
4. አባትና እናት በህይወት ባለመኖራቸው ወይም በሌላ ህጋዊ ምክንያት ቤተሰብን እንዲያስተዳድር በፍርድ ቤት የተሰየመ ሞግዚት ለቤተሰቡ ተጠሪ ይሆናል፤
5. ሌላ ቤተሰብ ሳይኖር እራሱን ችሎ ለብቻው የሚኖር ሰው የቤተሰቡ ተጠሪ ሆኖ ይመዘገባል፡፡

### 26.ስለ ሆሄያት ግድፈትና የዕድሜ ማስተካከል

1. አንድሰው በነዋሪነት ከተመዘገበ ወይም መታወቂያ ካገኘ በኋላ የስም ለውጥ ለማድረግ ጥያቄው የሚስተናገደው በፍርድ ቤት ቀርቦ የተወሰነ ከሆነ ብቻ ይፈፀማል፡፡
2. በነዋሪዎች መመዝገቢያ ቅጽ ወይም በነዋሪነት መታወቂያ  ላይ የፊደል ግድፈት ወይም የዕድሜ ማስተካከል ጥያቄ ሲቀርብ ማስተካከያው ለአንድ ጊዜ ብቻ ሆኖ፡-
   ሀ. ጥያቄው የሚስተናገደው እንዲስተካከልለት የተጠየቀው የፊደል ወይም የዕድሜ ትክክለኛነትን የሚያረጋግጥ በፎቶ ግራፍ የተደገፈና የተረጋገጠ ከሕጋዊ ተቋም የስራ መታወቂያ ወይም የትምህርት ማስረጃ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ ወይም የልደት ማስረጃ በማቅረብና በቃለ-መሀላ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ለ. ከላይ በተገለጸው መሠረት ማስረጃውንሲያሟላ እና አንድ ጊዜ ማስተካከያ ተደርጎ በድጋሜ ለሚጠይቅ ባለጉዳይ የሚሰጠው በፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረት ብቻ ይሆናል፣

ሐ. አንድ ሰውአስፈላጊውን ማስረጃ አቅርቦ እያለ የተፈጠረው የፊደል ግድፈት ወይም የዕድሜ ልዩነት በአገልግሎት ሰጪው ተቋም ባለሙያ ስህተት መሆኑ ሲረጋገጥ ያለምንም ቅድመ ሁኔታእዲስተካከል ይደረጋል፡፡

መ. ቀደም ብሎ የተመዘገበው ማስተካካያ የተደረገበትን ስም በቅጹ ላይ በአንድ ሰረዝ በማድረግ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሰረት የተስተካከለውን ስም ይጻፋል፡፡

## ክፍልሰባት

## የተከለከሉ ተግባራት

**27.በሠራተኛው እና በነዋሪው፡-**

1. **በሠራተኛው**

   ሀ. በከተማውለነዋሪዎች የነዋሪነት መታወቂያ ምስክር ወረቀት ከተዘጋጀውና በጽህፈት ቤቱ አማካይነት ከታተመውውጭ በሌላ መልኩ መታወቂያ መስጠት፤

   ለ. ለከተማው ነዋሪ ከከተማው ወረዳዎች ሌላ መታወቂያያላገኘ መሆኑን ሳያረጋግጥ መታወቂያ መስጠት፡፡

   ሐ. ነዋሪን ሲመዘግብ፣ ከምዝገባ በኋላ መታወቂያ ሲሰጥ ወይም ከዚያ በኋላ በቅጾችም ሆነ በኮምፒዩተር ላይ ስለ ነዋሪው መረጃ አላግባብ ስርዝ ድልዝ ወይም ለውጥ ማድረግ፡፡

2. **በነዋሪው፡-**

   ሀ. ማንኛውምየከተማ ነዋሪ ሆኖ የተመዘገበ ከአንድ በላይ የነዋሪነት መታወቂያ የምስክር ወረቀት ማውጣት ወይም ይዞ መገኘት ወይም፤

   ለ. አንድ ሰው ሐሰተኛ መረጃ በማቅረብ በነዋሪነት መመዝገበ ወይም የመታወቂያ ምስክር ወረቀት መውሰድ፤

**28.ስለተጠያቂነት**

1. በዚህመመሪያ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን የተላለፈ ሠራተኛ በዲስፕሊን ተጠያቂነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፤
2. አንድ ነዋሪ ከአንድ በላይ የነዋሪነት መታወቂያ አውጥቶ ወይም ይዞ የተገኘ እንደሆነ መታወቂያዎቹ ዋጋ እንዳይኖራቸው ተደርጎ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፤
3. በሐሰተኛ ሰነድ ወይም መረጃ በነዋሪነት የተመዘገበ ወይም ያስመዘገበመታወቂያ ያገኘ ወይም መታወቂያ እንዲያገኝ ያደረገ ምዝገባውም ሆነ የወሰደው መታወቂያመሰረዙ እንደተጠበቀ ሆኖበሐሰተኛ ሰነድ ወይም መረጃ የተጠቀመ ወይም እንዲጠቀም ያደረገ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

29.<u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው መመሪያዎች</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዋሪዎች አመዘጋገብ እና የነዋሪነት መታወቂያ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 1/2005 እና 2/2005፤
2. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቀበሌ አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር1/1996 ፤
3. ማንኛውም ልማዳዊ አሰርር እና ከዚህ መመሪያ የሚቃረን አሰራር ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

30. <u>መመሪያስለማሻሻል</u>

አስፈላጊ ሆኖ ከተገኝ ቢሮው መመሪያውን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

31. <u>መመሪያ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ጸድቆና ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ -----2010 ዓ.ም**

**ዮሐንስ ምትኩ**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ኃላፊ**

**ቅጽ 1**

**በአዲስ አበባ አስተዳደር ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ኤጀንሲ**

**የ………………. ክ/ከተማ ………… ወረዳ ወሳኝ ኩነቶች ቅ/ጽ/ቤት**

ቁጥር ……………………………ቀን …………………………….

ለ…………………………………………

<u>አዲስ አበባ</u>

1. መሸኛ ጠያቂው ስም ከነ አያት ………………………………………
2. ተወካይ ከሆነ የተወካይ ስም ከነአያት---------------------------------------------------የውክልና መዝገብ ቁጥር----------------------------
3. የእናት ስም፡- ………………………………………………….
4. የጋብቻ ሁኔታ፡- ያገባ/ች……….. ያላገባ/ች………… ፍቺ የፈጸመ/ች……….. በሞት የተለየ/ች……
5. ብሔር ………….
6. ዜግነት ………………….
7. አድራሻ፡- ክልል………. ክ/ከተማ/ዞን …… ወረዳ …….. ቀበሌ ……. የቤት ቁጥር ………
8. የትውልድ ዘመን፡- ቀን …….. ወር …… ዓ/ም……….
9. የትውልድ ቦታ፡- ክልል………… ዞን ………….. ወረዳ ………… ቀበሌ…….
10. የቤቱ ሁኔታ፡- የመንግስት ………… የግል ……………. ጥገኛ …………….
11. በወረዳው የቆዩበት ጊዜ፡- ……………………
12. ወረዳውን የለቀቁበት ምክንያት፡- ……………………………..……………………………..

| ተ.ቁ | የቤተሰብ ዝርዝር | የእናት ስም | የትውልድ ቀን | የትውልድ ቦታ | የጋብቻ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | | |
| 2 | | | | | |
| 3 | | | | | |
| 4 | | | | | |
| 5 | | | | | |
| 6 | | | | | |
| 7 | | | | | |
| 8 | | | | | |
| 9 | | | | | |
| 10 | | | | | |
| 11 | | | | | |
| 12 | | | | | |

በወረዳው ነዋሪ የነበሩ መሆናቸውን እየገለጽን ይህንን መሸኛ ስንሰጣቸው በእናንተ በኩል አስፈላጊው ትብብር እንዲደረግላቸው እንጠይቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ቅጽ 2

ቀን.........................................

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ኢጀንሲ

የ................... ክ/ከተማ ............ ወረዳ ወሳኝ ኩነቶች ቅ/ጽ/ቤት

<u>አዲስ አበባ</u>

<u>ለመታወቂያ ይሰጥልኝ በኃላፊነት ጠያቂ የሚሞላ የግዴታ ፎርም</u>

በክፍለ ከተማ ………….. ወረዳ ……… በቀድሞ ቀበሌ ……… የቤት ቁጥር ………. ነዋሪ የሆንኩኝ አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት ……………………………………… መታወቂያ ፈላጊ አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት……………………………….. የተባሉት በእኔ የቤተሰብ ቅጽ ላይ ተመዝግበው የነዋሪነት መታወቂያና አስፈላጊውን መረጃዎች እንዲሰጣቸው ስጠይቅ ተመዝጋቢው እኔጋ ከመጠምጣቱ /ቷ በፊት ይኖርበት/ትኖርበት የነበረው ወረዳ/ አካባቢ

ክልል ………… ክ/ከተማ/ዞን/ ………ወረዳ………ቀበሌ ……… የቤት ቁጥር…………..

ዜግነት …………………… የጋብቻ ሁኔታ ……………….. የእናት ስም ……………….

የትውልድ ቦታ ………………… የትውልድ ዘመን ቀን……. ወር ……ዓ/ም……………..

ፆታ ………….. የመተዳሪያ ስራ ……………………………

የነበሩ መሆናቸውን በሀላፊነትና በእውነት እንዲመዘገብለኝ ስጠይቅ ከላይ የተገለጸው መረጃ ሀሰት ሆኑ ቢገኝ እንዲሁም ያስመዘገብኩት ግለሰብ ዜግነቱ ከኢትዮጵያ ውጭ ቢሆን በሀገሪቱ ህግ ለመጠየቅ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 205 መስረት ግዴታ የገባሁ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ግዴታ የገባው አመልካች ሙሉ ስም ……………………………………

ፊርማ …………………………………..

_የተመዝጋቢ ግዴታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 205 መሰረት የቀረበ ቃለ-መሃለ_

እኔ አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት .............................................. በዛሬው እለት በ……………… ክ/ከተማ ወረዳ…….. በቀድሞ ቀበሌ ………… የቤት ቁጥር ………… በሆነው የነዋሪዎች ቅጽ ላይ ስመዘገብና የነዋሪነት መታወቂያ ስወስድ በየትኛውም ወረዳ የነዋሪነት መታወቂያ ያልወስድኩና የሌለኝ መሆኑንና አሁን በተመዘገብኩበት ቤት ውስጥ እየኖረኩኝና ሰላማዊ ሰው መሆኔን እንዲሆም ወረዳውን ስለቅ የወሰድኩትን የነዋሪነት መታወቂያ ለወረዳው የምመልስ መሆኑን አሁን የሰጠሁት ቃልና የግል መረጃዎቼ ትክክል መሆናቸውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 92 መሰረት በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

_ቃለ- መሀላ ተቀባይቃለ-መሀላ አቅራቢ_

የፈጻሚው ስም ……………………………

ፊርማ ……………………………………

የተመዝጋው ስም …………………………

ፊርማ ………………………………………

ፎርም 3

ቀን --------------------------

በ--------------------ክ/ከተማ ወረዳ------- ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ቅ/ጽ/ቤት

<u>የባለጉዳይ ማመልከቻ ፎርም</u>

- <u>ማሳሰቢ,ያየሚፈልጉትን አገልግሎት ያመላክቱ</u>

<u>አዲስ አበባ፡፡</u>

1ኛ. የነዋሪነት መታወቂያ

ሀ. አዲስ ------------ ለ. ዕድሳት ሐ. የጠፋ፣የተቀደደ፣የተበላሸ -------------

መ. የእድሜ እርማት --------------- ሠ. የፊደል ማስተካከያ -----------------------

ረ. መሸኛ---------------- ሸ. የነዋሪነት ምዝገባ-----------------------------

ቀ. የነዋሪነት ደብዳቤ------------------ ተ. ቅጽ ላይ ያለ መረጃ-------------------------

አመልካች

ሙሉስም---------------------------

ፊርማ ------------

<u>መታወቂያ የጠፋበት ግዴታ ፎርም</u>

እኔ አቶ/ወ/ሮ/ወ/ት ---------------------------------------------- በ----------------------ክ/ከተማ ወረዳ--------- በቀድሞ ቀበሌ-----------የቤት ቁጥር ------------ነዋሪ ስሆን ቀደም ሲል የወሰድኩት የነዋሪነት መታወቂያ የጠፋብኝ በመሆኑ በጠፋው የነዋሪነት መታወቂያ ስገለገልበት ብገኝ በወንጀል የምጠየቅ መሆኑን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 92 መሠረት ተጠያቂ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁኝ፡፡

ቃለ-መሐላ አቅራቢ

ሙሉ ስም --------------------------

ፊርማ--------------------

ፎርም 4

ቀን -------------------------

በ--------------------ክ/ከተማ ወረዳ------- ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ቅ/ጽ/ቤት

<u>አዲስ አበባ፡፡</u>

<u>የባለጉዳይ ማመልከቻ ፎርም</u>

1. የነዋሪነት ደብዳቤ ለ---------------------------------------
2. መሸኛ ለ--------------------ክልል---------------------ክ/ከተማ(ዞን) ወረዳ-------- .
3. አባትነት፣ እናትነት፣ እህትነት፣ ወንድምነት፣ አያትነት ለአቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት------------------ መሆኔን ተገልጾ ለ-----------------------------------መ/ቤት ደብዳቤ ይጻፍልኝ፡፡

አመልካች----------------------------------------

ሙሉ ስም--------------------------------------

ፊርማ---------------------------------------------

<u>የተገልጋዩ የማረጋገጫ ቃል፣</u>

እኔ አቶ/ወ/ሮ/ወ/ት --------------------------------------------- በ----------------------ክ/ከተማ ወረዳ--------- በቀድሞ ቀበሌ-----------የቤት ቁጥር ------------ነዋሪ ስሆን በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ቅ/ጽ/ቤት ቀርቤ የሰጠሁት መረጃ ወይም ማስረጃ እዉነተኛና ትክክል መሆኑን እንዲሁም ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ወይም ማስረጃ ሰጥቼ ብገኝ አግባብ ባለዉ የወንጀል ሕግ የምጠየቅ መሆኑን በማወቅ በፊርማዬአረጋግጣለሁ፡፡

ቃለ-መሐላ አቅራቢ

ሙሉ ስም --------------------------

ፊርማ-------------------